በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ/መ/ቁጥር
140284
ነሀሴ 30 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡- ክፍሉ ንጉሴ

ተጠሪ፡- የፌ/ጠ/ዐቃቤ ህግ

በወ/መ/ስ/ስ/ህ/ቁ.196 መሰረት አመልካች፡-ደፋሩ ደርቤ

መዝገቡ ለዛሬ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን በዚህ መሰረት ተመርምሮ የሚከተለው ብይን ተሰጥቷል

## ብይን

በወ/መ/ስ/ስ/ህ/ቁ.196 መሰረት አመልካች ሰኔ 29 ቀን 2014 ዓም በተፃፈ ባቀረቡት አቤቱታ አመልካች ባቀረበው የሰበር አቤቱታ አግባብ በስር ፍርድ ቤት የተሰጠው የቅጣት ውሳኔ ተሻሽሎ በቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 1/2002 አንቀፅ 16(8) መሰረት የቅጣት መነሻው እድሜ ልክ ፅኑ

ማ ስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

እስራት ለሆኑ ወንጀሎች ለእያአንዳንዱ የቅጣት ማቅለያ 3 እርከን የሚቀነስ መሆኑ መመልከቱን መሰረት ባመድረግ አመልካች ያቀረቧቸው ሁለት የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች ከግምት ውስጥ ገብተው የ18 አመት ፅኑ እስራት በመቀነስ በ15 አመት ፅኑ እስራት የተቀጣ በመሆኑ ይህ ውሳኔ ደግሞ በተመሳሳይ ሁለት የቅጣት ማቅለያ ላቀረብኩት በወ/መ/ስ/ስ/ህ/ቁ.196 መሰረት አመልካች ተግባራዊ ሊደረግልኝ ስለሚገባ ለአመልካች የተሠጠው ውሳኔ በወ/መ/ስ/ስ/ህ/ቁ.196(1)(ለ) መሰረት ተፈፃሚ ይህንልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡

በወ/መ/ስ/ስ/ህ/ቁ.196 መሰረት አመልካች ያቀረቡት አቤቱታ ለተጠሪ ደርሶት ሀምሌ 26 ቀን 2014 ዓም በተፃፈ ባቀረበው አስተያየትም የስር ፍርድ ቤት ከተቀበላቸው የቅጣት ማክበጃ ምክንያቶች አንፃር በማካካሻ አንድ እርከን ቢቀነስ ተቃውሞ የለንም በማለት አመልካች ካቀረበው የሰበር ክርክር አንፃር ክርክር አቅርበን አመልካች በ15 አመት ፅኑ እስራት እንዲቀጣ በ26/03/2010 ዓም የተወሰነ በመሆኑ፤ለአመልካች የተሰጠው ውሳኔ አቤቱታ አቅራቢውን የሚመለከትና የሚጠቅም በመሆኑ ፍርድ ቤቱ ካቀረብናቸውና የስር ፍርድ ቤት ከተቀበላቸው የቅጣት ምክንያች አንፃር በማካካሻ አንድ እርከን ተቀንሶ ቅጣቱ ቢቀል ተቃውሞ የለንም በማለት መልሱን አቅርቧል፡፡

እኛም እኛም በወ/መ/ስ/ስ/ህ/ቁ.196 መሰረት አመልካች ያቀረቡትን አቤቱታ ከተጠሪ መልስ እና ከተገቢው ህግ አንፃር እንደሚከተለው መርምረነዋል፡፡በመሰረቱ ለቅሬታ ሰሚው ፍርድ ቤት የቀረበው አቤቱታ ስለተፈረደባቸው ብዙ ሰዎች የሚመለከት ሆኖ ነገር ግን ቅሬታውን ያቀረበው አንድ ሰው ብቻ በሆነ ጊዜ በቀረበው ቅሬታ መሰረት የተሰጠው ፍርድ ለቅሬታ አቅራቢው የሚጠቅም ሆኖ በወ/መ/ስ/ስ/ህ/ቁ.196 መሰረት አቤቱታ ያቀረበውም ሊጠቀም ይችል ነበር የሚያሰኝ ሲሆን የተሰጠው ፍርድ ቅሬታቸውን ላላቀረቡትም ሰዎች በክርክሩ እንዳሉ ተቆጥሮ የሚፈፀምላቸው መሆኑ በወ/መ/ስ/ስ/ህ/ቁ.196(1) ተመልክቷል፡፡

አሁን በያዝነው ጉዳይ ይህ ችሎት ህዳር 26 ቀን 2010 ዓም በሰጠው ውሳኔ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠውን የቅጣት ውሳኔ በመመርመር በስር ፍርድ ቤት ተከሳሾች ካቀረቧቸው ሁለት የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች አንፃር በቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 01/2002 አንቀፅ 16(8) መሰረት አመልካች ጥፋተኛ ከተባሉት በዕድሜ ልክ ፅኑ እስራት ከሚያስቀጣው በወ/ህ/አ.671(2) ድንጋጌ አንፃር ለእየአንዳንዱ የቅጣት ማቅለያ 3 እርከን በድምሩ 6 እርከን ተቀንሶ አመልካች በእርከን 33 ስር በ15 ዓመት ፅኑ እስራት ሊቀጡ ሲገባ በ18 ዓመት ፅኑ እስራት መቀጣታቸው አግባብ አለመሆኑን በማመልከት በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠውን የቅጣት ውሳኔ በማሻሻል አመልካች በአስራ አምስት አመት ፅኑ እስራት እንዲቀጡ የወሰነ በመሆኑ በዚህ ውሳኔ ደግሞ በተመሳሳይ የወንጀል ድርጊት በተመሳሳይ ድንጋጌ ስር ጥፋተኛ የተባሉትና ተመሳሳይ የቅጣት ማክበጃ በተጠሪ

*ማ ሲታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ*
*ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም*

የቀረበባቸውና ተመሳሳይ የቅጣት ማቅለያ ምክንያት ያቀረቡት በወ/መ/ስ/ስ/ህ/ቁ.196 መሰረት አመልካች የሆኑት አቶ ደፋሩ ደርቤ በወ/መ/ስ/ስ/ህ/ቁ.196 መሰረት ሊጠቀሙ የሚገባ በመሆኑ በስር ፍርድ ቤቶች በወ/መ/ስ/ስ/ህ/ቁ.196 አመልካች ላይ የተጣለውን የቅጣት ውሳኔ በማሻሻል በወ/መ/ስ/ስ/ህ/ቁ.196 መሰረት አመልካች በዚህ ጉዳይ የታሰሩት ጊዜ ከግምት ውስጥ ገብቶ በአስራ አምስት አመት ፅኑ እስራት ሊቀጡ ይገባል በማለት ብይን ሰጥተናል፡፡

## ትዕዛዝ

ማረሚያ ቤቱ ከላይ በተመለከተው ብይን አግባብ የእስራት ቅጣቱን እንዲያስፈፅም የዚህ ብይን ግልባጭ ይተላለፍለት፡፡**መዝገቡ ተዘግቷል፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

አ/ኃ

*ማ ሳታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም*